## የመከላከያ ትዕዛዝ ምንድነው?

የመከላከያ / ጥበቃ / ትዕዛዝ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲሆን የቤት ውስጥ ጥቃት ፤ የወሲባዊ ጥቃት እና የማሳደድ / የክትትል ተጠቂዎችን ደህንነት ለማጠናከር የሚያገለግል ትዕዛዝ ነው። ይህ ትዕዛዝ ከሲቪል ጉዳዮች ጋር ወይም የተወሰኑ የወንጀል ክስ ጉዳዮች አካል ሆኖ ሊሰጥ ይችላል።

የወንጀል መከላከያ/ጥበቃ ትዕዛዞች የሚሰጡት እና ተፈጻሚ የሚሆኑት በወንጀል ክስ ጊዜ ብቻ ሲሆን፤ የትዕዛዙ ተፈጻሚነት ያለ ማስጠንቀቂያ በድንገት ሊያበቃ ይችላል። የሲቪል መከላከያ/ጥበቃ ትዕዛዝ ካስፈለግዎት ግን የወንጀል ክስ ጉዳይ ቢኖርም ባይኖርም ለመጠየቅ ይችላሉ። የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ እስከ አምስት ዓመት እንዲጸና ተደርጎ ሊታዘዝ እና በማሳደስም ሊራዘም ይችላል። በሒደት ላይ ያለ የወንጀል ክስ ካለ፤ የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ ከመጠየቅዎ በፊት ጠበቃዎን ያማክሩ። ምክንያቱም የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ መጠይቅዎ የሚያገኙትን ጥበቃ/ከለላ ሊያሳጣዎት እና የወንጀል ክሱ ውጤት ላይም ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል።

የሲቪል መከላከያ ትዕዛዞች በተለያየ መልክ ይታዘዛሉ። ይኸውም እንደደረሰው ወይም እየደረሰ ባለው የጥቃት ዓይነት እና ጥበቃ እንዲደረግልዎት ከሚፈልጉት ሰው ጋር እንዳለዎት የግንኙነት አይነት የተለያዩ ናቸው። ስለተለያዩ የሲቪል መከላከያ ትዕዛዝ ዓይነቶች ለመረዳት ፤ ለየትኛው የትዕዛዝ አይነት መስፈርት እንደሚያሟሉ እና ምን ዓይነት ከለላ/ጥበቃ ሊያገኙ እንደሚችሉ መረጃ ለማግኘት በ www.odvn.org/survivor/law.html ይመልከቱ።

## የመከላከያ ትዕዛዝ ያስፈልገኛል ወይ ?

ብዙውን ጊዜ ጥቃት ከሚያደርስብዎት ሰው ጋር ያልዎትን ግንኙነት ለማቆም ሲያስቡ ወይም ለመለያየት እርምጃዎችን ሲወስዱ የሚኖረው አደጋ ይጨምራል። የመከላከያ ትዕዛዞች የተወሰነ ከለላ እና ጥበቃ ሊሰጡ ይችላሉ። ነገር ግን ለደህንነት ፍጹም ዋስትና አይሰጡም ።

እንደዚሁም በተለይ ልጆች ካሉዎት፣ የሕግ ጉዳዮች ወይም በሌሎች ምክንያቶች አስቸጋሪ የሆነ የክስ ጉዳይ ካሉዎት፤ የመከላከያ ትዕዛዝ ለማግኘት ማመልከት ሌሎች ችግሮችንም ሊፈጥርብዎ ይችላል። ይሔውም የጥበቃ ትዕዛዝ በሚያስከትለው አደጋ /ያልተፈለገ ውጤት/ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት በ http://www.odvn.org/survivor/law.html ይግቡና እና "መጀመሪያ ጠበቃ ያስፈልገኛልን?" የሚለውን የማረጋገጫ ዝርዝር ያጠናቁ ።

በቤት ውስጥ ጥቃት ተሚጋች አጋዥነት የእራስዎን ግላዊ የደህንነት ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ለዚህም 800-934-9840 በመደወል በጣም ቅርብ የሆነውን የቤት ውስጥ ጥቃት ተሟጋች ፕሮግራም ማግኘት ይችላሉ። እንደዚሁም የጥበቃ ማዘዣ ለእርስዎ ትክክለኛ ውሳኔ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማጣራት ከቤት ውስጥ ጥቃት ተሟጋች ጋር መነጋገር ይችላሉ። የሕግ ባለሙያን ሳያማክሩ እና ምንም አይነት የደህንነት ዝግጅት ሳያደርጉ የመከላከያ ትዕዛዝ ማግኘት ደህንነትዎን ላያስጠብቅ ወይንም ለበለጠ አደጋ ሊያጋልጥዎ ይችላል።

odvn.org | 800-934-9840

## የሕግ ድጋፍ ስለማግኘት

አብዛኛውን ጊዜ በተለይ ጥቃት ከፈጸመብዎት ሰው ጋር ልጆች አፍርተው ከሆነ ወይም የሚጋሩት ንብረት ወይም እዳ ካለ፤ ክስ ከመመስረትዎ በፊት ጠበቃ ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው ። የሚከተሉት ጠበቃ እና የሕግ መረጃዎችን ማግኛ አማራጭ መንገዶች ናቸው።

- የሕግ ድጋፍ ሰጪ ቢሮዎች /Legal Aid Offices/፡- ነጻ የጠበቃ አገልግሎት በመስጠት ሊያግዝዎት ይችላሉ። የማህበረሰብዎን የሕግ ድጋፍ ሰጪ ቢሮ (Legal Aid Offices) ለማግኘት በ 866-529-6446 ይደውሉ ወይም በ www.ohiolegalhelp.org ይፈልጉ።
- የቤት ውስጥ ጥቃት መርሐግብሮች /Domestic Violence Programs/፡- የመከላከያ ትዕዛዝ ለሚያስፈልጋቸው የቤት ውስጥ ጥቃት ተጎጂዎች፣ገቢያቸው ምንም ይሁን ምን፣ ነፃ የሕግ አገልግሎት የሚሰጡ መርሐግብሮች አሉ። ተሟጋችዎ እርስዎን ከእነዚህ መርሐግብሮች እና ከወንጀል ተተቂ ካሳ መርሐግብር / Crime Victim Compensation Program) ጋር ሊያገናኝዎት እና እገዛን እንዲያገኙ ማድረግ ይኖርባቸዋል።
- ነፃ ጠበቆች / በጎ ፈቃደኞች /Pro Bono/ ፡- በአንዳንድ ማህበረሰብ ውስጥ በነፃ የሚያገለግሉ በጎ ፈቃደኛ ጠበቆች አሉ። ተሟጋችዎ ከታመነ/ሁነኛ ጠበቃ ጋር ሊያገናኝዎት ካልቻሉ፤ ከበጎ ፈቃደኛ ጠበቃ እገዛ ማግኘት ይችሉ እንደሆነ በአካባቢዎ የሚገኝ የሕግ ባለሙያዎች / ጠበቆች ማህበርን ማነጋገር ይችላሉ። እንደዚሁም በሚኖሩበት አካባቢ የሕግ ትምህርት ቤት ካለ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንዳላቸው ይጠይቁ።

የሕግ ምክር በመስጠት ወይም ጉዳይዎን ከፍርድ ቤት በማቅረብ ሊረዳዎት የሚችለው ጠበቃ ብቻ ነው። ተሟጋች ደግሞ ግላዊ የደህንነት ዕቅድ እንዲያወጡ ሊረዳዎት ይችላል፤ ይህም ለሚወስዱት ማንኛውም የሕግ እርምጃ አስፈላጊ አካል ነው።

Ohio Domestic Violence Network ODVN

The Ohio Domestic Violence Network (ODVN is a statewide coalition of domestic violence programs, supportive agencies, and concerned individuals working together to stop domestic violence through education, information and training for those who are affected by domestic violence, and by promoting social and systems change.

This project is supported by Grant No. G-1901OHSDVC awarded by the Department of Health & Human Services, Administration for Children and Families (ACF), Administration on Children, Youth, and Families (ACYF), Family and Youth Services Bureau (FYSB). The opinions, findings, conclusions, and recommendations expressed in this publication, program, exhibition are those of the author and do not necessarily reflect the views of the Department of Health & Human Services.

odvn.org | 800-934-9840

AMHARIC CPO BROCHURE

# የመከላከያ ትዕዛዝ ምንድነው?



Ohio Domestic Violence Network ODVN

## የመከላከያ ትዕዛዝ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

የመከላከያ ትዕዛዝ የማግኘት ሒደት በእያንዳንዱ ካውንቲ ውስጥ የተለያየ በመሆኑ እርስዎ በሚኖሩበት ካውንቲ ያለውን የአሰራር ሂደት ለማወቅ በአከባቢዎ የሚገኝ የቤት ውስጥ ጥቃት መርሐግብርን ያነጋግሩ። እንዲሁም ጠበቃ በማፈላለግ ወይም ለመከላከያ ትዕዛዝዎ አቤቱታዎን አሰናድቶ በማቅረብ እገዛ ሊያደርጉልዎም ይችሉ ይሆናል። የመከላከያ ትዕዛዝን ፋይል ለማስገባት ጠበቃ የግድ አስፈላጊ አይደለም፤ ነገር ግን ሂደቱ የተወሳሰበ ሊሆን ስለሚችል ሁል ጊዜ ጠበቃ መያዙ ተመራጭ ነው።በተለይ ጥቃት ከፈጸመብዎት ሰው ጋር ልጆች አፍርተው ከሆነ ወይንም ሌሎች የሕግ ጉዳዮች ካሉዎት፤ የመከላከያ ትዕዛዝን ለማግኘት አቤቱታዎን ከማስገባትዎ በፊት ጠበቃ ማማከር አስፈላጊ ነው። በአካባቢዎ ከሚገኝ የሕግ ድጋፍ ሰጪ ቢሮ /Legal Aid/ ፣የወንጀል ተተቂ ካሳ መርሐግብር /Crime Victim Compensation Program/ ወይም ሌሎች የነጻ ጠበቆች/በጎ ፈቃደኞች መርሐግብር /Pro Bono/ በኩል ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ሊያገኙ ይችላሉ። የመከላከያ ትዕዛዝ ለማመልከት የሚያስፈልግዎትን የወረቀት ፎርሞች ከሚያመለክቱበት ካውንቲ የፍርድ ቤቶች ጸሃፊ ዘንድ ያገኛሉ። በተጨማሪም እነዚህን ፎርሞች ከኦሃዮ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረገጽ (www.supremecourt.ohio.gov/JCS/domesticViolence/default.asp) ላይ ማውረድ ይችላሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ማንኛውንም ድረገጽ የሚጠቀሙ ከሆነ ጥቃት የሚፈጽምብዎት ሰው የማያገኘው፣በቤተ መጽሐፍት የሚገኝ ወይም የታማኝ ጓደኛዎን ኮምፒዩተር መጠቀም እንዳለብዎት አይርሱ።

## የፍርድ ቤት የአሰራር ሂደት ምን ይመስላል?

1ኛ ፡ አቤቱታ ማስገባት፡ - ተጠቂው ወይም ጠበቃቸው የመከላከያ ትዕዛዝ ስለመፈለጋቸው አቤቱታ ያቀርባሉ።

አስቸኳይ የመከላከያ ትዕዛዝ የሚያስፈልግዎት ከሆነ አቤቱታዎ የአንድ ወገን ብቻ አቤቱታ የሚሰማበት ችሎት ፍርድ ቤቱ እንዲሰይም አብሮ መጠየቅ ይኖርበታል ።

2ኛ ፡ የአንድ ወገን ችሎት /ex-parte/ ፡ - ፍርድ ቤት ደንቡ በሚፈቅደው የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ የአንድ ወገን

(ብቻ የሚገኝበትና) አቤቱታው የሚሰማበት ችሎት ይሰይማል። ለሲቪል መከላከያ ትዕዛዝ ሲሆን አቤቱታው በሚገባበት ቀን የሚከናወን ይሆናል። ከማሳደድ/ክትትል እና/ወይም ከወሲብ ጥቃት ጋር የተያያዘ መከላከያ ትዕዛዝ ከሆነ፣ ወይም ከወጣት/ታዳጊ ጥፋተኛ ጋር የተያያዘ መከላከያ ትዕዛዝ ሲሆን የአንድ ወገን ችሎት አቤቱታው በሚገባበት ቀን ወይም በሚቀጥለው የፍርድ ቤት ቀጠሮ እለት የሚሰየም ይሆናል። ይህ ለእርስዎ ለምን አስቸኳይ የጥበቃ ትዕዛዝ እንደፈለጉ ለዳኛው ለማስረዳት ዕድል የሚሰጥዎት ሲሆን፣ ትዕዛዙን መስጠት ወይም ላለመስጠት የሚወስነው ዳኛው ይሆናል።

3ኛ ፡ ክስ ማሳወቂያና መጥሪያ ስለመላክ፡ - ለተከሳሽ (ጥበቃ እንዲደረግልዎት ለሚያመለክቱበት ሰው) ያስገቡት

የማመልከቻ ቅጅ ፣ የመከላከያ ትዕዛዙ ቅጅ (በአንድ ወገን ችሎት ተወስኖ የተሰጠ ከሆነ) እና ሙሉ ችሎት የሚሰማበትን ቀን የሚገልጽ መጥሪያ እንዲደርሰው ይደረጋል ። ይህ ጊዜ ለደህንነትዎ አደገኛ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም የደህንነት እቅድዎ ተጨማሪ ጥንቃቄዎችን ማካተት አለበት።

4ኛ ፡ ሙሉ ችሎት /full hearing/ ፡ - ፍርድ ቤቱ ከ 7- 10 ቀናት ውስጥ የሁለት ወገን ክስ የሚሰማበትን

ቀን ይቆርጣል። በዚህ ቀን የግድ መቅረብ ይኖርብዎታል። በዚህም ቀን ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፡- ክስ የመስማቱ ሂደት በሌላ ቀን እንዲካሄድ ሊተላለፍ ይችላል፤ እርስዎና ምላሽ ሰጪው /ተከሳሽ/ በመከላከያ ትዕዛዙን በተመለከተ የመግባባት ስምምነት ላይ ሊደርሱ ይችላሉ ወይም ደግሞ ችሎቱ ሊካሄድ ይችላል ።

በሚቀጠሩበት በማንኛውም የችሎት ቀን ምስክርዎችዎን፣ ማስረጃዎችዎን እና በአቤቱታዎ ውስጥ ያካተቱትን ሁሉንም ነገሮች ይዘው ለመቅረብ ዝግጁ መሆን አለብዎት። በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ የልጆች ጠባቂነትን እና ልጆች መጠየቂያ ጊዜን፣ አደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነትን እና የኑሮ ሁኔታን ወዘተ በተመለከተ መረጃዎች እንዲቀርቡለት ሊፈቅድ/ሊጠይቅ ይችላል።

5ኛ፡ - የፍርድ ቤት ትዕዛዝ - ፍርድ ቤቱ ችሎቱ በሚሰማበት ቀን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል ወይም ጊዜ ወስዶ

ትእዛዙን ደብዳቤ በመላክ ሊያሳውቅ ይችላል፡፡ የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ጠንካራ ሊሆን ይችላል። ይሄውም - መልስ ሰጪ / ተከሳሽ / የት ሊሆን እንደሚችል / ከከሳሽ እንዴት መራቅ እንዳለበት/ ፣ ልጆችን የመጠበቅና የመንከባከብ መብት የማን እንደሚሆን ፣ በቤቱ ውስጥ ማን ሊኖርበት እንደሚችል እና መልስ ሰጪው /ተከሳሹ / የጦር መሳሪያ ለመያዝ ፈቃድ ወይም እግድ መኖሩን ሁሉ የሚያዝ ሊሆን ይችላል ። እንደዚሁም ፍርድ ቤቱ የጥበቃ ትዕዛዝ ጥያቄዎን ውድቅ ሊያደርግ / ሊከለክል / ይችላል ፤ ይህ ደሞ ቀጣይ ደህንነትዎን አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ እንዲወድቅ ያደርገዋል።

የመከላከያ ትዕዛዝዎ ሁል ጊዜ ከእርስዎ መለየት የለበትም ምክኒያቱም በድንገት ለፖሊስ ደውለው ትእዛዙን እንዲያስከብርልዎ መጠየቅ ሊያስፈልግዎ ይችላል። እንደዚሁም ከልጅዎ ትምህርት ቤት፣ ከስራ ቦታዎ ወይም ትእዛዙ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ሁሉ ትእዛዙን ቅጂ መስጠት አለብዎት።

## ከፍርድ ቤት ችሎት በፊት የሚያደርጉት ዝግጅት

- ወደ ፍርድ ቤት እንዴት እንደሚሄዱ እና (አስፈላጊ ከሆነም) ስለ መኪና ማቆሚያ ቦታ ማወቅ አለብዎት። ለማንኛውም የፍርድ ቤት ቀጠሮ ከቀጠሮው ሰዓት በፊት ቀድመው ለመድረስ ያቅዱ።
- በፍርድ ቤት ውስጥ በንፅህና እና ስርዓት ባለው መልካም ገጽታ መቅረብ አስፈላጊ ነው።
- በፍርድ ቤት ቆይታዎ፣ በችሎት ጊዜ እና ከችሎት በፊት ወይም በኋላ ከተከሳሹ (ተነጥለው) ሳይገናኙ የት መቆየት እንዳለብዎት ከተሟጋችዎ እና ጠበቃዎ ጋር በቅድሚያ ያቅዱ። ተከሳሹ ከእርስዎ ጋር የማይፈለጉ ግንኙነቶችን ለማድረግ ከሞከረ ወይም ከፍርድ ቤት ለመውጣት የሚያጅብዎት ከፈለጉ የፍርድ ቤቱን ሠራተኞች እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ።
- ልጆችዎን በምስክርነት የሚያቀርቡ ካልሆነ በስተቀር ወደ ፍርድ ቤት ማምጣቱ አይመከርም። ችሎቱ የሚወስደው ጊዜ አጭር ወይም ረጅም ሊሆን ስለሚችል ልጆችዎን የት እንደሚያቆዩ በቅድሚያ ማቀድ አልብዎት። የሕፃናት ማቆያ እና መንከባከቢያ ለማግኘት ካልቻሉ ከተሟጋችዎ ጋር ይማከሩ።
- ለእያንዳንዱ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ከመቅረብዎ በፊት፣ ያስገቡትን አቤቱታ፣ ማመልከቻ እና ማስረጃዎች መመለከት እና ጉዳዮን በሚገባ ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ምስክሮችዎም የሚቀርቡ መሆናቸውን እና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የፍርድ ቤት መጥሪያ የደረሳቸው መሆኑን ያረጋግጡ።
- ለሁሉም ፍርድ ቤት ቀጠሮች ሲገኙ ከተሟጋችዎ ጋር የመቅረብ ሕጋዊ መብት አለዎት።
- እንግሊዝኛ ቋንቋ የማይናገሩ ከሆነ፣ መስማት የተሳኖት ከሆኑ ወይም የመስማት ችግር ካለብዎ፣ በፍርድ ቤቱ የሚመደብ የቋንቋ አስተርጓሚ የማግኘት መብት አለዎት። አስተርጓሚ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ማመልከቻዎን በሚያስገቡ ጊዜ እንደዚሁም የፍርድ ቤት የቀጠሮ ቀን በተቀየረ ጊዜ ሁሉ ለተሟጋችዎ እና ለፍርድ ቤቱ ያሳውቁ። ለሁሉም ችሎቶች ከጠበቃ ጋር መቅረቡ ተመራጭ ነው።

odvn.org | 800-934-9840

## ምስክርነት ለመስጠት የሚጠቅሙ ምክሮች

- እውነታን አጥብቅው በመያዝ የተጠየቁትን ጥያቄ ብቻ ይመልሱ። ተጨማሪ ማብራሪያ / መረጃ መስጠት ከፈለጉ፣ተራዎን እንደገና ጠብቀው መናገር ሊኖርብዎት ይችላል።
- ዳኛው እና የፍርድ ቤቱ ዘጋቢ ለመስማት እንዲችሉ ድምፅዎን ከፍ አድርገው በግልፅ ይናገሩ።
- ትርጉማቸውን በሚገባ የማያውቋቸውን ቃላቶች ፣ ለምሳሌ የሕግ ወይም የሕክምና ቃላቶችን፣ ከመጠቀም ይቆጠቡ።
- ለጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ ጊዜዎን ወስደው፣ አስበው ይመልሱ። ጥያቄው ካልገባዎት ወይም የጥያቄውን መልስ ካላወቁት በግልጽ ይናገሩ። ምን እንደተጠየቁ በሚገባ ካልተረዱ በስተቀር መልስ አይስጡ።
- በፍርድ ቤት ውስጥ ስነምግባር እና ጥንቃቄ የተሞላበት ባህሪን ያሳዩ፣ እንደዚሁም ሁል ጊዜም ዳኛው/ዋን ሲጠሩ “የተከበሩ ዳኛ” ብለው ይጥሩ።
- ተከሳሽ ወይም የተከሳሽ ጠበቃ እርስዎን ሊያበሳጭ ወይም ሊያስቆጣ የሚችሉ ነገሮችን ሊናገሩ ይችላሉ። እርስዎ ስሜትዎን በመቆጣጠር ተረጋግተው ለመቆየት ጥረት ያድርጉ። እረፍት ማድረግ ካስፈለግዎትም ዳኛውን ይጠይቁ ።

## የመከላከያ ትእዛዙ ቢጣስስ?

የመከላከያ ትዕዛዝዎ በሁሉም የአሜሪካ ስቴቶች ውስጥ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። ትዕዛዝዙ ከተጣሰ ደህንነትዎን የበለጠ ለማጠናከር ከተሟጋች ጋር በዕቅዶችዎ ላይ ይነጋገሩ። በተጨማሪም የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ።

- ከትዕዛዙ ጥሰት ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ማስረጃ ይሰብስቡ። ይህ ለምሳሌ ጥቃት ፈጻሚውን ፣ የጥቃት ፈጻሚውን መኪና እና በንብረት ላይ የደረሰን ጉዳት ፎቶግራፍ ማንሳት ያካትታል። እንደዚሁም የጽሑፍ ወይም የስልክ መልዕክቶችን ፣ በማህበራዊ ሚዲያ የተቀመጡ መልዕክቶችን ወይም ኢሜይሎችንም መያዝ ይጨምራል።
- ለፖሊስ በመደወል የጥበቃ ትዕዛዝዎን / ተከሳሹን በቁጥጥር ስር በማዋል / እንዲያስከብርልዎት ይጠይቁ። የመከላከያ ትዕዛዝን መጣስ በወንጀል የሚያስጠይቅ ጥፋት ሊሆን ይችላል። ለፖሊስ ሲደወሉ በተቻለ ፍጥነት የትእዛዙ ጥሰት እየተፈጸመ ባለበት ወቅት ወይም እንደተፈጸመ ይሁን። ፖሊስ ተከሳሹን በቁጥጥር ስር ካላዋለ፣ ጥፋቱ / ጥሰቱ / ተመዝግቦ ሪፖርት እንዲደረግ ይጠይቁ ።
- ትዕዛዙ በተጣሰበት አካባቢ የአቃቤ ሕግ ዘንድ በመሄድ የወንጀል ክስ ስለ መመስረት ይነጋገሩ።
- መጀመሪያ የመከላከያ ትዕዛዝ ለሰጠዎት ፍርድ ቤት ተከሳሽ የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ባለማክበር ሕግን እንደተላለፈ የሚገልጽ አቤቱታ ያስገቡ።

Ohio Domestic Violence Network
ODVN